מדינת ישראל
משרד החינוך
מינהל פדגוגי
אגף א' שרות פסיכולוגי ייעוצי

# ለዉድ ወላጆች ያለንበት የደህንነት ሁኔታ

**ዉድ ወላጆች ፡**

ዛሬ ጥዋት በሕዝበ እስራኤል ልይ ተወንጫፊ ምሳየሎች እየተተኮሱ ነዉ ከንቅልፋችን ያነቃን ይህ ዉስብስብ እና አስጊ ሁኔታ ነገ ምን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ ስለማይቻል የወላጅ ሐላፊነት በአሁኑ ሰዓት የደጀን መመርያን መከተል ይሆናል ። በእንደዚህ ባለ ጊዜ ልጆች ህጻናት ወይንም ታላላቅ ልጆች ፍርሀት ሊሰማቸዉ ይችላል ስለዚህ ወላጅ እንደመሆናችን መጠን ልጆቻቸሁን አይዞችሁ በርቱ በማለት ከጎናቸዉ ሁናችሁ እንድታበረታቱ ፡ የልጆችን ደህንነት ብዙ እንደሜሳስባችሁ በመገንዘብ ልንመክራችሁ የምንፈልገዉ ምንም ነገር ቢሆን ወይም ቢፈጠር ልጆች በሚረዱት ቋንቋ በግልጽ እና ባጭሩ ያለዉን ሁኔታ ማስረዳት እና ማጠናከር የጸባይ ለውጥ ቢታይ ትግስተኛ በመሆን ማዳመጥ እና ከጎናቸዉ መሆን ይገባል

ከዚህ በመቀጠል የተወሰነ ይጠቅማሉ ብለን የምናምንባቸዉን ነጥቦች እናቀርባለን ፡ ግልጽ ያልሆኑ ጥያቄወች እና ግራ የመጋባት ሁኔታ ቢኖር ወላጅ እንደመሆናችሁ መጠን በእራሳችን መተማመን እና ዉስጣችን የሜምንበትን ዉሳኔ መቀበል ወሳኝ ነዉ ።

በዚህ ዉስብስብ እና አስፈሪ የጦርነት ጊዜ ልጆች እና ወጣቶች ከወላጆቻቸዉ ብዙ ይጠብቃሉ ፡ ይህ ጊዜ በጣም ዉድ እና ወሳኝ መልክቶችን የምናስተላልፍበት ጊዜ ስለሆነ ሙሉ ጊዜያችሁን እንድትሰጧቸዉ እና ያለንበትን ሁኔታ እንደ እድሜችው በማመዛዘን ልናረጋጋችዉ ይገባል ።

<u>የድንገተኛ ጊዜ መመርያ መርሆዎች ፡</u>

**ትክክለኛ መልክት ማስተላለፍ ፡**

በእስራኤል የጦር ደጀን የሚተላለፉትን መመሬያወች እና ጊዜያዊ መልክቶችን ማዳመጥ እና መተግበር ተገቢ ነዉ ።

ወላጆች ለልጆቻቸዉ የሰሙትን መልክት በጥሩ ሁኔታ እና በተረጋጋ መንፈስ ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል

ወላጆች እራሳቸዉን በመጠበቅ እና ጥንቃቄ በማድረግ ለልጆቻቸዉ ምሳሌ ይሆናሉ ይህ መሆኑ ልጆች በወላጆቻችው እንዲተማመኑ ይረዳል

**የደህንነት የስራ ሂደት ማስታወስ ፡** ከሁሉም በላይ ለልጆች ማስተማር እና ማስገንዘብ የሚገባን የማስጠንቀቂያ ደወል ሲሰማ በፍጥነት ወደ መጠጊያ ቦታ እንዲገቡ ማስተማር እና ቦታዉን ማሳየት ወሳኝ ሲሆን በዚህ ጊዜ መሆን የሚገባቸዉን ቅደም ተከተል እንዲፈጽሙ ማስተማር ይገባናል ።

**መልክት እና እዉነታዉን መረዳት ፡** ስላለዉ የደህንነት ሁኔታ ለልጆች በሚገባችዉ ቀላል እና ግልጽ በሆነ ቋንቋ ማስረዳት እንጅ ተጨንቆ ልጆችን እንዲጨነቁ ማድረጉ ጉዳት አለዉ በተለይ ዉድ ወታደሮቻችን የአገራችን እና የህዝባችን ደህንነት እንደሚጠብቁ ማስተማር እና ማሳወቅ

**የስራ ድርሻ መፍጠር ፡** ባለንበት የደህንነት ሁኔታ ልጆች እንዳይሰለቻቸዉ እና በፍርሀት እንዳይጨነቁ እንደ እድሜቸዉ መጠን በስራ እንዲጠመዱ ማድረግ እና የመጫወቻ አይነቶችን ማዘጋጀት ።

የቀን ከቀን ተግባርን መፈጸም ፡ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት ወይም መዋዕለ- ህጻናት እንዲሄዱ ማበረታታት ያስፈልጋል። ይህ የሚሆነዉ የእስራኤል የደህንነት ክፍል በሚያስተላልፈዉ መልዕክት መሰረት መሆን አለበት ።

**ልጆች ሃሳባቸዉን ለሌሎች እንዲያካፈሉ መገፋፋት ፡**ልጆች ሃሳባቸዉን ስሜታቸዉን እንዲያሳትፉ መገፋፋት ወሳኝ ሲሆን ወላጆችም ለልጆቻቸዉ ስሜታቸዉን በማይጎዳ ሁኔታ የሚሰማቸዉን ማካፈል ይቻላል ።

**ፍርሀት እና ጭንቀት ላለባቸዉ ልጆች መደረግ ስለሚገባቸዉ ቅድመ ዝግጅት ፡**

ልጆችም ሆነ ጎልማሶች ሁኔታወችን የሚረዱት በተለያየ መልኩ ነዉ ይህም ሲባል አንድ አንድ ልጆች በተፈጥሮቸዉ አስተያየታቸዉ የበለጠ ስሜታዊ በመሆናቸዉ የተነሳ ከወላጆች የሚጠበቀዉ ልጆች በራሳቸዉ ችሎታ እንዲተማመኑ መንገር እና ማበረታታት ፍርሃትን መቋቋም እንዲችሉ ይረዳቸዋል ።

እያንዳንዱ ልጅ የመረዳት ችሎታው የተለያየ በመሆኑ አስፈላጊዉን እርዳታ በሰዓቱ መለገስ ወይም የስራ ባለሙያ በመጠየቅ እርዳታ እንዲሰጣቸዉ ጥረት ማድረግ ይገባል ።

**የትምህርት ክፈል ሃላፊን ማሳወቅ ፡**ከልጆች መምህራን ጋር ጥሩ ግንኙነት ሊኖረን ይገባል ምክንያቱም አስፈላጊ ሲሆን በተለይ ባደጋ ጊዜ ትኩረት በመስጠት እንዲንከባከቡት ይረዳል

**ብቸኝነትን አለመምረጥ ፡** አሁን ያላችሁበት ወቅት የስሜት መረበሽ መጨናነቅ ላይ ከሆናችሁ እና ጥያቄወች ካላችሁ ብቸኝነት አይሰማችሁ ፤ እርዳታ ለመቀበል የትምህርት አማካሪዋንም ሆነ የስነልቦና ባለሙያ በማማከር እርዳታ መቀበል ይቻላል።

**መልካም የሰላም እና የተረጋጋ ጊዜ እንዲሆንልን እንመኛለን !!!**

**የስነልቦና እና የምክር ባልሙያወች -**

**ከትምህርት ሚንስተር**